# ሃጎስ ሃጎስ ይላል ፣ ግድግዳና አጥሩ

ሁሉም አንድ ሆነሳ ፣ ስም ጠፋ ወይ ባገር
ቋንቋው አንድ ሆነብኝ ፣ ሁሉም ሰው ሲናገር
ሃስትም አይደለ ፣ ስሙ እስኪ ስናገር
ሰው ባእድ ይሆናል ፣ ባደገበት አገር
በሄድኩበት ስፍራ ፣ ሁሉም ሃጎስ ነበር ።

ከመከላከያ ፣ ጎራ ብል ደርሼ
ከበታች መኮንን ፣ እስከላይ ዳስሼ
የወታደሩን እዝ ፣ ሁሉንም አምሼ
ከሃጎስ በስተቀር ፣ ስላጣሁ ነቅሼ
በወሰደኝ እግሬ ፣ ወጣሁ ተመልሼ ።

በለመደው እግሬ ፣ ደህንነት ገብቼ
የተሻለ ይሆናል ፣ በማለት ገምቼ
ማጣራት ጀመርኩኝ ፣ መዝገቤን አውጥቼ
    ግና ምን ያደርጋል ፣ አልሆነም ያሰብኩት
    የተለየ ነገር ፣ አገኛለሁ ያልኩት
    ሁሉም ሃጎስ ሆኑ ፣ ጭራሽ ያልጠበቅኩት ።

ለምናልባት ብዬ ፣ ከጉምሩክ ብገባ
ይገኙ እንደሆነ ፣ ተገኝ እና ሮባ
ካንዱ ቢሮ ወዳንዱ ፣ ብወጣ ብገባ
ሁሉም ሃጎስ ብቻ ፣ ሞክቶ የሰባ
ምኑን አሳየሽኝ ፣ ጆሮም ልበስ ዳባ
ተሰፋዬ በቀለ ፣ የሚል ስም የት ገባ ።

ከቤተ ክህነቱ ፣ አየር መንገድ ብሄድ
ከሃጎስ በስተቀር ፣ አይታይ በመንገድ
    ትምህርት ሚኒስቴር ፣ ማረሚያን ጎብኝቼ
    ከሃጎስ በስተቀር ፣ ሌላ ስም አጥቼ
እስቲ ለምናልባት ፣ ወጥቼ ከምድሩ
አየር ተሳፍሬ ፣ ብዞር በየሃግሩ
ይገኙ እንደሆነ ፣ ቶሎሳና ፍቅሩ
በር በማንኳኳት ፣ ኢምባሲ መዞሩ
የሚፈታ መስሎኝ ፣ የሃጎስ ሚስጥሩ
ከታችኛው ሎሌ ፣ እስካምባሳደሩ
እንኳን አምባሳደር ፣ ዘበኛው የበሩ
ሃጎስ ሃጎስ ይላል ፣ ግድግዳና አጥሩ
ካሳሁን በለጠ ፣ ዲማና መገርሳ ፣ የሉም በሀገሩ ።

ታዛቢው

December 24, 2017